" ግንበኞች የናቁት ድንጋይ:- እርሱ የማዕዘን እራስ ሆነ፣
ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች:- ለዓይናችንም ድንቅ ናት። "
መዝ.117 ቁ.22-23

# ኦ ባ ማ

**ኦባማ ኦባማ ኦባማ ኦባማ**
**ነፃነት ለራበው ፍትህ ለተጠማ...**

ምድሪቱ ጨቅይታ
ተበክላ በደም
በዘር በሃይማኖት
ሲጨፋጨፍ ዓለም
ግፍ ሞልቶ ፈሶ
ቢወጣ ከሰማይ
የአምላክ ዓይን አረፈ
መርጦት ኦባማ ላይ።

**ኦባማ ኦባማ ኦባማ ኦባማ**
**ነፃነት ለራበው ፍትህ ለተጠማ...**

እስላምም የአባቱ
ክርስቲያን የእናቱ
ነጭም በደሙ ውስጥ
ጥቁር መሠረቱ።

አምላክ አዋቂ ነው
ሲመርጥ ሚበጀንን
ከትንቢያ አንስቶ
ኦባማን ቀባልን።

**ኦባማ ኦባማ ኦባማ ኦባማ**
**ነፃነት ለራበው ፍትህ ለተጠማ...**

ግንበኞች የናቁት
የተጣለ ድንጋይ
በኛ ዘመን አየን
ሆኖ ከሰው በላይ።

ዳዊት እረኛውን
ያነገሠ አምላክ
ኦባማን ላከልን
ተደገመ ታሪክ።

የዘመናት ባሮች እንበል ቀና ቀና
ኦባማን እናግዝ ውጥኑ እንዲቃና።

**ኦባማ ኦባማ ኦባማ ኦባማ**
**ነፃነት ለራበው ፍትህ ለተጠማ...**

**ከየአፅብአሔ**
**በርን - ስዊትዘርላንድ- 8/11/ 2008**